ዓባይ ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር

Abay Construction PLC

# የትራክ ማውንትድ ክሬን እና የውሃ መገጣጠሚያ እቃዎች ግዥ የጨረታ ሰነድ

## ብሄራዊ ግልጽ ጨረታ (NCB)

መጋቢት/2017 ዓ/ም

**ብሄራዊ ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ**

የጨረታ ቁጥር አኮኃ/የተ/የግ/ማ/ብግጨ**/07/17**

አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **ትራክ ማውንትድ ክሬን እና የውሃ መገጣጠሚያ እቃዎች ግዥ በብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።**

**ስለሆነም ድርጅቱ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾችን ይጋብዛል።**

1. **በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የቫት ምዝገባ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፤**
2. **የሚገዙ ዕቃዎች ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ ከጨረታ ሰነዱ ማግኘት ይቻላል።**
3. **ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን አማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ** 16 **ድባንቄ መድሀኒያለም ቤተክርስቲያን ህዳሴ ሰፈር ታክስ ማዞሪያ** 190 **ሜትር እልፍ ብሎ** አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **ቢሮ ከግዥ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር** 19 **የማይመለስ ብር** 200 **/ሁለት መቶ ብር/ በመክፈል ማግኘት ይቻላል።**
4. **ተጫራቾች ለሚወዳደሩባቸው ዕቃዎች** 2% **የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና** (Bid Bond) **በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ** (CPO) **ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና** (Unconditional Bank Guarantee) **በ**አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **ስም ማስያዝ አለባቸው።**
5. **ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተገለፀው መሰረት የጨረታውን ሰነድ በታሸገ ፖስታ ትክክለኛ ስምና አድራሻ በመፃፍ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ *ለ15 ተከታታይ ቀናት እስከ 15ኛው ቀን 8፡00 ሰዓት* በስራ ሰዓት ከግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር** 19 **በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይችላሉ።**
6. **ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ**15**ኛው ተከታታይ ቀን ከቀኑ በ**8፡00 **ሰዓት ይዘጋል ፤በ**15**ኛው** ተከታታይ ቀን **ከቀኑ** 8፡30 **ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር** 19 **ይከፈታል።**
7. **15**ኛው ተከታታይ **ቀን የበዓላት ቀን ከሆነ ጨረታው በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል።**
8. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።**
9. **በጨረታው ለመሳተፍ ለሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር** 19 **ድረስ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ቁጥር** ***https:/www.abayconstruction.org.et/auction-bid/*** 058 38304460/ 0991021430 **በመደወል ማግኘት ይችላሉ።**

**ድርጅቱ**

## ይዘት ገጽ


የተጫራቾች መመሪያ ........ 1

1. ጠቅላላ ........ 1
2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል ........ 1
3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /Bid Bond/ እና የውል ማስከበሪያ ........ 2
4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ እና የውድድር ሁኔታ ........ 2
5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ ........ 3
6. ራስን ከጨረታ ስለማግለል ........ 3
7. ጨረታ መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊ መለየት ........ 4
8. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ ........ 4
9. የመጫረቻ ሰነድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ ........ 5
10. የጨረታ ውጤትን ስለመግለጽና የውል ስምምነት ስለመግባት ........ 5
11. የማቅረቢያ ቦታ ........ 5
12. የውል ማስከበሪያ ........ 6
13. የአቅርቦት መጠን ........ 6
14. አቤቱታ ስለማቅረብ ........ 6


አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር
Abay Construction PLC
ቁ.5

# <u>የተጫራቾች መመሪያ</u>

## 1. ጠቅላላ

1.1. የግዥ ፈፃሚው መ/ቤት ሙሉ አድራሻ አማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ ቀበሌ 16 **ድባንቄ መድሀኒያለም ቤተክርስቲያን ህዳሴ ሰፈር ታክስ ማዞሪያ 190 ሜትር እልፍ ብሎ ፡፡**

1.2. ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት የሚገዛቸው ዕቃዎች **ትራክ ማውንትድ ክሬን እና የውሃ መገጣጠሚያ እቃዎች** ናቸው፡፡

1.3. **ተጫራቾች ከመጫረቻ ሰነዳቸው ጋር የታደሰ** የንግድ ስራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የምስክር ወረቀት **ማቅረብ አለባቸው።**

1.4. በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ከአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከሚዘጋበት ቀን ድረስ ዘወትር በሥራ ሰዓት መውሰድ ይችላሉ፡፡

1.5. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ማንኛውንም ዓይነት ግብር የሸፈነ መሆን አለበት፡፡

1.6. ድርጅቱ (ግዥ ፈጻሚው) ከክፍያው ላይ የሚቀንሰው 2% ዊዝሆልድ ታክስ ብቻ ነው፡፡

1.7. ተጫራቾች በወጣው የጨረታ ሰነድ ላይ ጥያቄ ወይም ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 058 38304460/0991021430 በመደወል ወይም በጽሁፍ ጨረታው ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ማቅረብ አለባቸው፡፡ ግዥ ፈጻሚውም እስከ 10ኛው ቀን ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

1.8. ተጫራቾች በሚያቀርቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ሠነድ ላይ ሙሉ ስማቸውን የስልክ፣ የፋክስና የመልዕክት ሣጥን ቁጥራቸውን መጻፍ ይኖርባቸዋል፡፡

1.9. ዋጋ የሚሞሉት በአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር በተዘጋጀው ቅጽ ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡ ይሁን እንጂ በራሳቸው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ለመጠቀም የሚፈልጉ ተጫራቾች ካሉ መ/ቤቱ በተሰጣቸው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ ላይ የተመለከቱትን በጥንቃቄ ወደ ራሳቸው ቅጽ ማስፈር አለባቸው፡፡ በዚህ ወቅት የመረጃ መዘለል ቢፈጠር የተጫራቹ ሰነድ ከውድድር ውጭ የሚደረግ መሆኑ በቅድሚያ ሊታወቅ ይገባል፡፡

1.10. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## 2. የጨረታ ሰነድ ስለማሻሻል

2.1. አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር **ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ እስከ 10ኛው ቀን ድረስ በሥራ ሰዓት በራሱ ወይም የጨረታ ሰነዱን በገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መነሻነት የጨረታ ሰነዱን ማሻሻል ይችላል። ከ10ኛው ቀን በኋላ ለቀረበ ማብራሪያ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ አይገደድም።**

2.2. የተደረገው ማሻሻያ የጨረታ ሰነዱ አካል የሚሆን ሲሆን በጽሁፍ ተዘጋጅቶ ሰነዱን ለገዙ እጩ ተወዳዳሪዎች እና በቀጣይ ሰነዱን ለሚገዙ ሁሉ በተገቢው ሁኔታ በእኩል ጊዜ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

2.3. በጨረታ ሰነዱ ማሻሻያ መሠረትም አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የጨረታ መክፈቻ ጊዜውን እንደ አስፈላጊነቱ አስከ 5 ተከታታይ ቀናት ሊያራዝም ይችላል፡፡

2.4. ተጫራቾች ቀደም ሲል ባስገቡት የጨረታ ዋጋ ላይ ማሻሻያ በማድረግ በልዩ ሁኔታ መቀነስ ቢፈልጉ ቅድመ ሁኔታ ባልተቀመጠበት አግባብ ካቀረቡት ዋጋ የሚቀንሱትን መጠን በመቶኛ (%) የጨረታው ሳጥን እስከሚዘጋበት ሰዓት ብቻ ፊርማና ማህተም ተደርጎበት ማስገባት ይችላሉ፡፡ ሆኖም የዋጋ ቅናሹ የግልጽ ጨረታ ሥርዓትን የማይጋፋ መሆን አለበት፡፡

## 3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /Bid Bond/ እና የውል ማስከበሪያ

3.1. ተጫራቾች ለሚወዳደሩበት የብር መጠን 2% የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /bid bond/ በCPO ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረት የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ***<u>ከዋጋ ማቅረቢያ (ከፋይናንሺያል ሰነድ)</u>*** ጋር በጥንቃቄ በታሸገ ፖስታ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

3.2. ከተጫራቾች የሚቀርበው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ፀንቶ መቆያ ጊዜ ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለ60 ቀናት ጸንቶ መቆየት ይኖርበታል፡፡

3.3. ተሸናፊ ተጫራቾች ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ጨረታው ተከፍቶ አሸናፊው ተለይቶና ውል ከተያዘ ጀምሮ ባሉት በ6 ወራት ውስጥ መውሰድ አለባቸው፡፡

3.4. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ይወረሳል፡፡

ሀ. የጨረታ ማስከበሪያው ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተጫራቹ ራሱን ከውድድር ካገለለ፤

ለ. አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለፀለት በኋላ ውሉን ለመፈረም ፈቃደኛ ሆኖ ካልተገኘ፤

ሐ. አሸናፊው እንዲያቀርብ የተጠየቀውን የውል ማስከበሪያ 10% ካላቀረበ፤

መ. ተጫራቹ ጨረታውን ለማዛባት የሞከረ መሆኑ በማስረጃ ከተረጋገጠ፤

3.5. ከላይ በተ.ቁ 3.4 /ሀ-ሠ/ ከተመለከቱት አንዱን የፈፀመ ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ሙሉ ለሙሉ የሚወረስበት ሲሆን በህግም ሊጠየቅ ይችላል፡፡

3.6. የውል ማስከበሪያ(performance bond) ላሸነፉበት ዕቃ 10% በCPO ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 4. የመጫረቻ ሰነድ አቀራረብ እና የውድድር ሁኔታ

4.1. ተጫራቾች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ፎቶ ኮፒ እና የሚያቀርቡትን የመጫረቻ ሰነድ በጨረታ ሰነዱ የተመለከተውን የዕቃ ዋጋ ማቅረቢያ ቅፅ በመጠቀም በተገለፀው ዝርዝር መግለጫ (Detail specification) መሠረት ሰነዳቸውን ስርዝ ድልዝ በሌለበት ሁኔታ ተለይቶ በጥንቃቄና በዝርዝር በመሙላት በመፈረምና በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ማህተም በማድረግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስርዝ ድልዝ ካለም ስለመስተካከሉ ፊርማቸዉን በማስቀመጥ /ፖራፍ/ በማድረግ መረጋገጥ አለበት፡፡

4.2. የጨረታ አቀራረብን በተመለከተ፡-

- ሎት01 በተለያየ ሁለት ፖስታ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ኦሪጅናል፣
- ሎት02 በአንድ ፖስታ ቴክኒካልና ፋይናንሻል ኦሪጅናል፣

4.3. ውድድርን በተመለከተ **በየሎቱ በእያንዳንዱ የእቃ አይነት በነጠላ ዋጋ** አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

4.4. በማሸጊያ ፖስታ ላይ የሚከተሉትን ነጥቦች ማስፈር ያስፈልጋል፡፡

ሀ. የጨረታው ዓይነትና ቁጥር፣..........................

ለ. ጨረታውን ያወጣው መስሪያ ቤት ስምና አድራሻ፣..................................

ሐ. የተጫራቹ ስም፣ ስልክ ቁጥር፣ ፊርማና ሙሉ አድራሻ፣.........................

4.5. በፖስታ የሚላክ የመጫረቻ ሰነድ በመዘግየቱና በጥንቃቄ ካለመታሸጉ ጋር በተያያዙ ችግሮች ግዥ ፈጻሚው መ/ቤት ኃላፊነቱን አይወስድም፡፡

## 5. የመጫረቻ ሰነድ ማቅረቢያ የጊዜ ገደብ

5.1 ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ ከተገለፀው የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት በፊት የመጫረቻ ሰነዱን በተዘጋጀው የጨረታ ቦታ እና የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም **ተጫራቾች የመጫረቻ ሰነዶቻቸው ብዛት ያላቸው ከሆኑና በጨረታ ሳጥኑ ውስጥ ማስገባት አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ በድርጅቱ የግዥ የሥራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 በመገኘት ለተመደበው ግዥ ኦፊሰር ማስረከብ ይችላሉ። ተረካቢውም የተጫራቹን ስምና አድራሻ እንዲሁም የተረከበበትን ቀንና ሰዓት በመመዝገብ ለመረከቡ ማረጋገጫ (ማስረጃ) የሚሰጥ ሲሆን በግዥ ኦፊሰር የተሰበሰቡ የመጫረቻ ሰነድ ፖስታዎችን ጨረታው ከመዘጋቱ 30 ደቂቃ በፊት ለግዥና ጨረታ ኮሚቴው ርክክብ ያደረጋል።**

5.2 በጨረታ ሰነዱ መሰረት የመጫረቻ ሰነድ ማስረከቢያ የመጨረሻ ቀንና ሰዓት ደርሶ የጨረታ ሳጥን ከተዘጋ በኋላ የሚቀርብ የመጫረቻ ሰነድ ተጫራቹ በአካል ከቀረበ በተጫራቹ እጅ እንዳለ በሌላ አግባብ የመጣ ከሆነም ሳይከፈት ለተጫራቹ /ለአቅራቢው/ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## 6. ራስን ከጨረታ ስለማግለል

6.1 **ተጫራቾች የጨረታ ሳጥኑ ከመዘጋቱ ቀንና ሰዓት በፊት ራሳቸውን ከጨረታው ማግለል ይችላሉ። ስለሆነም ራሳቸውን ከጨረታው ስለማግለላቸው በሚያቀርቡት ሰነድ ላይ የድርጅቱ ህጋዊ ማህተም ማድረግና ሙሉ ስማቸውን መጻፍ ይኖርባቸዋል። የጨረታ ሰነዱን የሚሞሉና የሚፈርሙ ተወካዮች ከሆኑ ሕጋዊ የውክልና ማስረጃቸውን የተገናዘበ ፎቶ ኮፒ ከሚቀርበው ሰነድ ጋር በማያያዝ በፖስታ አሽገው የጨረታ ሳጥኑ ከመዘጋቱ በፊት በጨረታ ሳጥኑ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።**

6.2 የጨረታ መዝጊያ ጊዜ ከተጠናቀቀ በኋላ ተጫራቾች ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሃሳብ ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ ማድረግና ከጨረታው ራሳቸውን ማግለል አይችሉም፡፡

## 7. ጨረታ መክፈት፣ መገምገምና አሸናፊ መለየት

7.1. የጨረታው አየር ላይ ቆይታ **15** ተከታታይ ቀናት ሲሆን ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን ከቀኑ 8፡30 ሰዓት በመ/ቤቱ የግዥ የስራ ሂደት ቢሮ ቁጥር 19 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት በግልፅ ይከፈታል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ጨረታው በሚከፈትበት ቦታ፣ ቀንና ሠዓት በራሳቸው ምክንያት ባይገኙ ጨረታው እንዲከፈት በማድረግ ውድድሩ ይካሄዳል፡፡

7.2. ጨረታዉ ሲከፈት በንባብ የሚሰሙ የተጫራቾች ሥም፣ የተወዳደረበት ምድብ (ሎት)፣ የሚደረግ የዋጋ ቅናሽ ካለ መጠኑንና ሁኔታውን በሚመለከት (ቅድመ ሁኔታ ያልተቀመጠበት እና የጨረታ ሥርዓቱን የማይጋፋ መሆኑን)፣ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ዓይነትና መጠን እንዲሁም ሌሎች እጩ ተወዳዳሪዎች ደረጃቸውን ለማሳወቅ ይረዳቸዋል ተብለው የሚታሰቡ መሰረታዊ ነጥቦች በጨረታው መክፈቻ ወቅት ለተጫራቾች ይነበባሉ፡፡

7.3. በግዥ ፈጻሚ መ/ቤቱ የቀረቡትን የጨረታ ሰነዶች በመገምገም ሂደት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከተጫራቾች ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚጠየቀውና የሚሰጠው ማብራሪያ በሁሉም ተጫራቾች እንዲታወቅ በፅሁፍ ሆኖ ተጫራቾች ካቀረቡት

የመወዳደሪያ ሃሳብ ውስጥ ዋጋውን ወይም የሌሎች መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን እንዲለወጡ ማለትም በሌሎች ተፎካካሪ አቅራቢዎች ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ መሆን የለባቸውም፡፡

7.4. በግምገማ ወቅት በነጠላ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋ መካከል የዋጋ ልዩነት ቢኖር በነጠላው ዋጋ መሠረት በማስተካከል ይገመገማል፡፡

7.5. በግምገማ ወቅት ዋጋው በአኃዝና በፊደል በሚገለጽበት ወቅት ልዩነት ቢኖር በፊደል በተገለጸው መሠረት በማስተካከል ይገመገማል፡፡

7.6. ከተጠየቀው ዝቅተኛ መስፈርትና ከዚያ በላይ ቴክኒካል መስፈርቱን የሚያሟሉ ተጫራቾች መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው አሸናፊ ይመረጣል፡፡

7.7. ወድድሩ ቴክኒካል መስፈርት አሟልቶ በእያንዳንዱ እቃ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች አሸናፊ ሆኖ ይመረጣል፡፡

## 8. ጨረታን ውድቅ ስለማድረግ

8.1 በጨረታ የተወዳደረው አቅራቢ ግዥ ፈፃሚው መ/ቤት የፈለገውን አነስተኛ የጥራት መመዘኛ መስፈርት ያላሟላ በመሆኑና ብቃት የሌለው ሆኖ ሲገኝ፤

8.2 ተጫራቹ በአንዱ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋው መካከል የሂሳብ ስህተት ማስተካከያ የማይቀበል ሲሆን፤

8.3 ተጫራቹ ያቀረበው የመጫረቻ ሰነድ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ያላሟላ ሆኖ ሲገኝ፤

8.4 በተራ ቁጥር 1.2 የተዘረዘሩትን የጽሁፍ ማስረጃዎች እንዲሁም በተጨማሪ ሌላ ተፈላጊ የሙያ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ተጠይቆ ከጨረታ ማቅረቢያ ሰነዱ ጋር ወይም በበቂ ምክንያት በጨረታ ግምገማ ወቅት ማቅረብ ካልቻለ፤

8.5 ተጫራቾች የግዥ አካሄዱን ለማዛባት በመመሳጠራቸው በቂ ውድድር አለመደረጉ ሲረጋገጥ፤

8.6 የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ተጠይቆ ያላስያዘ እንደሆነ፤

8.7 ተጫራቾች ዋጋ አቀራረብ/አሞላል እና የምድብ/የሎት ምርጫን በሚመለከት በተጠየቀው መሰረት ሞልተው ካላቀረቡ፡፡

8.8 የአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር የግዥ መመሪያ እና ይህን የጨረታ ሰነድ የሚጥሱ ድርጊቶች መፈፀሙ የተረጋገጠ ከሆነ፤

## 9. የመጫረቻ ሰነድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ

9.1 የመጫረቻ ሰነድ እስከ 60 ቀናት ድረስ ፀንቶ ይቆያል፡፡

9.2 ግዥ ፈጻሚ መስሪያ ቤት የመጫረቻ ሰነዱ ጸንቶ የሚቆይበትን ጊዜ እንዲራዘምለት ከፈለገ ዕጩ ተወዳዳሪዎችን በጽሁፍ በመጠየቅ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡ ሆኖም ዕጩ ተወዳዳሪዎች ካልተስማሙ ያስያዙትን የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) መውረስ ሳያስፈልግ ከጨረታው ዉድድር እንዲሰረዙ ይደረጋል፡፡

9.3 የቀረበላቸውን የመጫረቻ ሰነድ የመቆያ ጊዜ ማሻሻያ ጥያቄ የተቀበሉ ተጫራቾች መቀበላቸውንና ጊዜውን በመጥቀስ በጽሁፍ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለዚህ ጨረታ ያስያዙት ዋስትና መቆያ ጊዜ አብሮ እንዲሻሻል ማድረግ ወይም አዲስ ዋስትና ማቅረብ አለባቸው፡፡ የጨረታ ዋስትናውን ያላሻሻለ ተጫራች የጨረታ ሰነዱን ለማሻሻል ፈቃደኛ እንዳልሆነ ተቆጥሮ ከጨረታው ውጭ ይደረጋል፡፡

## 10. የጨረታ ውጤትን ስለመግለጽና የውል ስምምነት ስለመግባት

10.1 ማንኛውም የጨረታ ግምገማ ውጤት በሚመለከታቸው አካላት በጸደቀ በዕለቱ ለተመረጡ በአድራሻቸው በደብዳቤ እና በውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ የሚገለጽ ሲሆን ላልተመረጡ ተጫራቾች ደግሞ በውስጥ የማስታወቂያ ሰሌዳ ያልተመረጡበትን ምክንያት በማካተት በእኩል ጊዜ ለሁሉም ይገለጻል፡፡

10.2 አሸናፊው ተጫራች አሸናፊነቱ ከተገለጸለት ቀን ጀምሮ እና የግዥ ውል እንዲፈጽም ከአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ደብዳቤ በደረሰው ከ3 የስራ ቀናት የቅሬታ ጊዜ በኋላ ባሉት 5 የስራ ቀናት ውስጥ 10% የውል ማስከበሪያ በሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በማስያዝ የዕቃ አቅርቦት ውል ከግዥ ፈጻሚ መ/ቤት ጋር መፈራረም አለበት፡፡

10.3 በጨረታ አሸናፊ የሆነው ተጫራች የአቅርቦት ውል ለመፈረም ፈቃደኛ ካልሆነ ያስያዘውን የጨረታ ማስከበሪያ በመውረስ ከሌሎች ፈቃደኛ ከሆኑ ተጫራቾች ጋር በየደረጃቸው ቅደም ተከተል በአንደኛው ዋጋ ውል በመያዝ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይቻላል፡፡

10.4 በጨረታው አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው አቅራቢ ድርጅት **በሎት 1 የተጠቀሰው ትራክ ማውንትድ ክሬን በሚፈለገው ስፔስፊኬሽን እና በቀረበው ሞዴል** መሆኑን በባለሙያ ተረጋግጦ ርክክብ የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## 11. የማቅረቢያ ቦታ

11.1 የማቅረቢያ ቦታ በውል ጊዜው የተዘረዘሩትን እቃዎች **በሎት 1** እና **በሎት 2** የተጠቀሱት እቃዎች ባህር ዳር ከተማ ከሚገኘው ከግዥ ፈጻሚው መ/ቤት (አባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) መጋዘን ይሆናል፡፡

## 12. የውል ማስከበሪያ

12.1 **አሸናፊ ተጫራቾች ማቅረብ ያለባቸው የውል ማስከበሪያ መጠን** ያቀረቡትን ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ (ፐርፎርማንስ ቦንድ) በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ /CPO/ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (unconditional bank guarantee) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

## 13. የአቅርቦት መጠን

13.1 **በጨረታ ሰነዱ ላይ የተጠየቀውን የዕቃ መጠን በውል ወቅት እስከ 20% በመጨመር ወይም በመቀነስ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከውል በኋላ እስከ 30% ተጨማሪ የግዥ ትዕዛዝ በመስጠት ግዥ መፈጸም ይቻላል።**

## 14. አቤቱታ ስለማቅረብ

14.1 በጨረታ ሂደቱ ጉዳት ወይም ኪሳራ ደርሶብኛል የሚል ወይም በጨረታው ግምገማ ውጤት ቅር የተሰኘ ማንኛውም ተጫራች ጨረታው እንደገና እንዲታይለት የጨረታ ውጤት ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ሥራ አስኪያጅ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

14.2 አቤቱታ የቀረበበት መ/ቤትም ምላሹን በቀረበለት በ3 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለአቤቱታ አቅራቢው መልስ ይሰጣል፡፡

14.3 በአባይ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር ስራ አስኪያጅ ውሳኔ ያልረካ አቅራቢ በፍርድ ቤት ክስ ሊመሰርት ይችላል፡፡

14.4 በተራ ቁጥር 14.1 ከተሰጠው ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ማንኛውም አቤቱታ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

| | Lot -01 5.5Ton Track Mounted Crane | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **No** | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | **የተመረተበት አገር** (Country of Origin) | **የምርቱ መጠሪያ ስም** (Brand Name) | **ሞዴል** (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
| 1 | 5.5 Ton Track Mounted Crane | 5. 5 ton capacity Track mounted crane.<br>. Lifting capacity of the crane minimum 5.5 ton.<br>. Loading capacity of the track minimum 10ton.<br>. Drive type—left hand<br>. minimum speed—70km/hr.<br>Engine (fundamental)<br>. Type –4stroke, diesel engine<br>. number of cylinder…6 in line<br>. power out put… .220HP around 1800rpm.<br>Other detail spesfications attached with the bid document other page. | pcs | 01 | | | | | | |

- የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም
- አድራሻ ……
- የማስረከቢያ ቦታ አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ
- ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት
- ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው፡

| | Lot -02 Pipe and Fittings | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
| 1 | GI pipe 2 1/2" medium class (B-class) | GI 21/2" medium class riser pipe sa per BS1387 L=6m | Pcs | 39 | | | Fershao wsp |
| 2 | GI coupling C- class | Heavy class 21/2"coupling Beded type | Pcs | 36 | | | >> >> |
| 3 | Flanaged water meter | DN 65mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 4 | CI Double Flanged Gate valve | DN 65mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 5 | CI Double Flanged Gate valve | DN50mm pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 6 | CI Double Flanged non return valve(check valve) | DN65mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 7 | Double flanged GS elbow $90^{o}$ | DN65mm pn16 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 8 | Presure Gage Glycrine filled 0-25bar | 0-25bar with isolated cock& 1/2" male socket out let | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 9 | Dismanteling joint | DN65mm pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 10 | GS Double flanged Reducer Tee, | DN65/50/65mm pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 11 | GS Double flanged GS elbow $90^{o}$ | DN50mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 12 | GS well head cover | flange 14", hole 80mm at the center | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 13 | CI Double flanged single orfice Air realse valve | DN50mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 14 | Bolt Nut with washer | M16*100*1.15mm | Pcs | 96 | | | >> >> |
| 15 | Flat Gasket | DN65 , pn16 | Pcs | 12 | | | >> >> |
| 16 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 110mm,PN 16 | Pcs | 1 | | | >> >> |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | Flat Gasket | DN50 pn16 | Pcs | 6 | | | >> >> |
| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
| 18 | GS Thresded Flange | DN65mm pn16 | Pcs | 10 | | | Fershao wsp |
| 19 | Gs threaded Flange | DN50mm pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 20 | GS double flanged Reducer | DN100/65mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 21 | Bolt Nut with washer | M-20,L=130mm | Pcs | 717 | | | ሰሃላ ፕሮጀክት |
| 22 | Bolt Nut with washer | M-16,L=130mm | Pcs | 1200 | | | >> >> |
| 23 | Flat Gasket | DN100mm,pn10 | Pcs | 179 | | | >> >> |
| 24 | Flat Gasket | DN150mm,pn10 | Pcs | 26 | | | >> >> |
| 25 | Flat Gasket | DN200mm, pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 26 | HDPE Buttweld ,stub flanged Adapter with Back ring | OD 110mm, pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 27 | DCI Double flanged 90$^o$ elbow | DN200mm, pn10 | Pcs | 14 | | | >> >> |
| 28 | DCI Double flanged 90$^o$ elbow | DN150mm,pn10 | Pcs | 10 | | | >> >> |
| 29 | HDPE Buttweld 45$^o$ elbow | OD160mm,pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 30 | HDPE Buttweld 90$^o$ elbow | OD160mm,pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 31 | HDPE Buttweld reducer | OD160/110mm, pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 32 | HDPE Buttweld reducer | OD200/160mm, pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 33 | GS Flanged Back ring Adapter | DN150mm,pn10 | Pcs | 10 | | | >> >> |
| 34 | GS Flanged Back ring Adapter | DN200mm, pn10 | Pcs | 34 | | | >> >> |
| 35 | CI Double flanged Dismanteling joint | DN200mm, pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 36 | CI Double flanged Dismanteling joint | DN150mm,pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 37 | CI Double flanged Dismanteling joint | DN100mm,pn10 | Pcs | 5 | | | >> >> |
| 38 | CI Double Flanged Gate valve | DN200mm, pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 39 | CI Double Flanged Gate valve | DN150mm,pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 40 | CI Double Flanged Gate valve | DN100mm,pn10 | Pcs | 20 | | | >> >> |
| 41 | CI Double Flanged Water meter | DN200mm, pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 42 | CI Double Flanged Water meter | DN150mm,pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 43 | CI All flanged Equal Tee | DN200mm, pn10 | Pcs | 1 | | | ሰሃላ ፕሮጀክት |
| 45 | GS All flanged Equal Tee | DN100mm,pn10 | Pcs | 8 | | | >> >> |
| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
| 46 | GS Flanged Reducer Tee | DN100/50/100mm, pn10 | Pcs | 108 | | | ሰሃላ ፕሮጀክት |
| 47 | GS Flanged Reducer Tee | DN200/100/200mm, pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 48 | CI Double flanged stainless steel strainer | DN200mm, pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 49 | Automatic Level guage | Automatic Level guage | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 50 | GI Pipe medium class(B-class | 1" B-class, L=6m | Pcs | 7 | | | >> >> |
| 51 | GI Pipe medium class(B-class) | 1 1/2" B-class, L=6m | Pcs | 120 | | | >> >> |
| 52 | GI Pipe medium class(B-class) | 2" B-class, L=6m | Pcs | 7 | | | >> >> |
| 53 | GS Pipe medium class(B-class) | 4" B-class, L=6m | Pcs | 23 | | | >> >> |
| 54 | GS Flanged end plug | DN100mm,pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 55 | GS Double flanged 90º Elbow | DN100mm,pn10 | Pcs | 12 | | | >> >> |
| 56 | GS flange | DN100mm,pn10 | Pcs | 27 | | | >> >> |
| 57 | GS Internally Threaded flange | DN100mm,pn10 | Pcs | 9 | | | >> >> |
| 58 | GS medium class welded type coupling | DN100mm,pn10 | Pcs | 6 | | | >> >> |
| 59 | Gi pipe 2" Low class (A-class) | Light class 2" Pipe L=6meter | Pcs | 3 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 60 | Gi pipe3" Medium class (B-class) | Medium class 3" Pipe L=6meter | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 61 | Gi pipe6" Medium class (B-class) | Threaded Medium class 6" Pipe L=6meter | Pcs | 8 | | | >> >> |
| 62 | Gi threaded Coupling 6" medium class | 6" Buded type medium class socket coupling | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 63 | Gs threaded Flange | DN 80mm pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 64 | Gs threaded Flange | DN 80 mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 65 | Gs threaded Flange | DN 100mm pn10 | Pcs | 7 | | | >> >> |
| 66 | Gs threaded Flange | DN 100mm pn16 | Pcs | 6 | | | >> >> |
| 67 | Gs threaded Flange | DN 150mm pn10 | Pcs | 27 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 68 | DcI blind flange | DN 150mm pn10 Blind | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 69 | Flat Gasket | DN 80mm pn 16 | Pcs | 8 | | | >> >> |
| 70 | Flat Gasket | DN 80mm pn 10 | Pcs | 7 | | | >> >> |
| 71 | Flat Gasket | DN 100mm pn 10 | Pcs | 13 | | | >> >> |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 72 | Flat Gasket | DN 100mm pn 16 | Pcs | 12 | | | >> >> |
| 73 | Flat Gasket | DN 150mm pn 10 | Pcs | 52 | | | >> >> |
| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
| 74 | Bolt Nut with washer | M8*60*1.15mm | Pcs | 4 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 75 | Anchor Bolt | M12*1200*1.15mm | Pcs | 20 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 76 | Bolt Nut with washer | M16*100*1.15mm | Pcs | 316 | | | >> >> |
| 77 | Bolt Nut with washer | M20*120*1.15mm | Pcs | 480 | | | >> >> |
| 78 | DCI flanged Elbow $90^o$ | DN 80mm pn16 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 79 | DCI flanged Elbow $90^o$ | DN 100mm pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 80 | GSI Double Flanged Elbow $90^o$ | DN 150mm pn10 | Pcs | 7 | | | >> >> |
| 82 | CI Double Flanged Water meter | DN 150mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 83 | CI Double Flanged Gate valve | DN 150mm pn10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 84 | CI Double Flanged Check valve | DN 150mm pn10 | Pcs | 3 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 85 | Pressure Guage ,glycrine filled 0-10 Bar | glycrine filled 0-10 Barwith Isolating cock & 1/2" male socket out let | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 86 | Pressure Guage ,glycrine filled 0-16 Bar | glycrine filled 0-16 Barwith Isolating cock & 1/2" male socket out let | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 87 | Pressure switch working range of 0-16 bar | range of 0-16 bar with Isolating cock &1/2" male socket out let | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 88 | CI double Flanged Dismanteling Joint | DN 80 mm ,pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 89 | CI double Flanged Dismanteling Joint | DN 100 mm ,pn10 | Pcs | 2 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 90 | CI double Flanged Dismanteling Joint | DN 150 mm ,pn10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 91 | CI double Flanged Reducer Tee | DN 100x80x100 mm ,pn16 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 92 | CI double Flanged Reducer Tee | DN 150x80x150 mm ,pn10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 93 | GS Double flanged $90^o$ Elbow | DN 80 mm ,pn10 | Pcs | 1 | | | ሰሀላ መጠጥ ውሃ |
| 94 | CI double Orfice Flanged Air Relse Valve | DN 80 mm ,pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 95 | CI double Flanged strainer | DN 150mm ,pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 96 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD355/90/355pn10 | Pcs | 1 | | | ታላቅ ወንዝ ፕሮጀክት |
| 97 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD200/90/200pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 98 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD180/90/180pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 99 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD180/75/180mm pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 100 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD160/75/160mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 101 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD160/63/160mm pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 102 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD140/110/140mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 103 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD140/75/140mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 104 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD125/110/125mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 105 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD125/75/125mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 106 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD110/63/110 mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 107 | HDPE Buttweld equal Tee | OD63/63/63 mm pn10 | Pcs | 1 | | | >> >> |
| 108 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 50mm,PN 10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 109 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 63mm,PN 10 | Pcs | 10 | | | >> >> |
| 110 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 75mm,PN 10 | Pcs | 12 | | | >> >> |
| 111 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 160mm,PN 10 | Pcs | 8 | | | >> >> |
| 112 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 200mm,PN 10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 113 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 400mm,PN 10 | Pcs | 16 | | | >> >> |
| 114 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD400/40/400mm pn10 | Pcs | 4 | | | >> >> |
| 115 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD400/50/400mm pn10 | Pcs | 2 | | | >> >> |
| 116 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD400/63/400mm pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 117 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD355/63/355mm pn10 | Pcs | 5 | | | >> >> |
| 118 | HDPE Buttweld reducer Tee | OD140/40/140mm pn10 | Pcs | 3 | | | >> >> |
| 119 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 110mm,PN 10 | Pcs | 6 | | | >> >> |

| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ ቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ቫት ጋር | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 120 | HDPE stub flange Adapter with back ring | OD 125mm,PN 10 | Pcs | 4 | | | ታላቅ ወንዝ ፕሮጀክት |
| 121 | GS Flanged Butter flay gate valve | DN 1000mm diameter PN 10 with full accessories | Pcs | 02 | | | Taba soil dam |
| 122 | GS Flange | DN 1000mm, pn10 | Pcs | 04 | | | Taba soil dam |
| 123 | Water stop | made of natural or synthetic rubber or elastomeric plastic compound with basic risen polyvinyl chloride (PVC)width25cm,*4mm thickness | Meter | 1026 | | | Alwadi,enezer,marza,Ledeta ,shala projects |
| | Total price | | | | | | |

- የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም
- አድራሻ ……
- የማስረከቢያ ቦታ አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ
- ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት
- ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው፡

| | Lot -03 Automatic Leveling with staff guage | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| No | የእቃው አይነት | ዝርዝር መግለጫ | መለኪያ | ብዛት | የተመረተበት አገር (Country of Origin) | የምርቱ መጠሪያ ስም (Brand Name) | ሞዴል (Model) | የአንዱ ዋጋ ከቫት ጋር | ጠቅላላ ዋጋ ከቫት ጋር | ምርመራ |
| 1 | Automatic Leveling staff guiage | Telescope:<br>. Length… ≥214mm<br>. Magnification ..≥24X<br>. Objective… ≥32mm<br>. Resolving power… ≤4”<br>.Field of view … 1°25’(25m at 100m) | pcs | 01 | | | | | | Detail spesfication attached with in the document |

- የተወዳዳሪው ድርጅት ሙሉ ስም
- አድራሻ…………
- የማስረከቢያ ቦታ አባይ ኮንስትራክሽን መጋዘን ድረስ
- ዋጋ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ -ለ60 ቀናት
- ድርጅቱ ተቀናሽ የሚያደርገው 2% (ዊዝሆልዲንግ) ታክስ ብቻ ነው